# የኤጲፋንዮስ የሃይማኖት ውሳኔ

1) ዓለምን ኹሉ ፈጥሮ በሚገዛ፥ የሚታየውን የማይታየውንም ኹሉ በፈጠረ፥ በአንድ አምላክ በአብ እናምናለን።

2) ከአብ በተወለደ፥ በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን። ቅድመ ዓለም ከአብ ባሕርይ ተወለደ። በኋላ ዘመንም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ከኀጢአት ብቻ በቀር ለሰው ያለውን ኹሉ ነፍስን፥ ሥጋን፥ ልብን፥ ዕውቀትን፥ ገንዘቡ ያደረገ ፍጹም ሰው ሆነ። በዘርዐ ብእሲ የተወለደ አይደለም፤ በሰው ኹሉ እንደሚያድርም አላደረበትም፤ እርሱ ሥጋን ነሥቶ ለእርሱም ለብቻው ገንዘብ አደረገው እንጂ፤ በተዋሕዶም አንድ አደረገው እንጂ። ዐድሮ እንደ ተናገረባቸው እንደ ነቢያት ኹሉ አይደለም፤ ፍጹም ሰው ሆነ እንጂ። ቃል ሥጋ ሆነ፥ አልተለወጠም፥ መለኮቱን ሰው ወደ መሆን አልለወጠውም፥ ከመለኮት ጋር ጽኑዕ አንድነቱን በተዋሕዶ አደረገ እንጂ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው፥ ፈጣሪ ነው፥ ንጉሥ ነው፥ በሥጋ ሞቶ የተነሣ እርሱ ነው፥ በዚሁ አንድ አካል ወደ ሰማይ ዐረገ፥ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በዚሁ አንድ አካል ይመጣል።

3) ሕግን በሠራ፥ በነቢያት ዐድሮ ባስተማረ፥ በዮርዳኖስ በወረደ፥ በሐዋርያት ዐድሮ ባስተማረ፥ በቅዱሳንም ባደረ፥ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። ባሕርየ መንፈስ ቅዱስ ያልተፈጠረ፥ ከአብ የተገኘ፥ ቃልነትን ከወልድ ገንዘብ ያደረገ፥ ፍጹም አካላዊ እንደ ሆነ በእርሱ እናምናለን።

4) ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

5) ንስሓ ለመግባትና ኀጢአትን ለማስተስረይ የምትሰጥ ጥምቀት አንዲት እንደ ሆነች እናምናለን።

6) ለሙታን የምትደረግ ትንሣኤ አንዲት እንደ ሆነች እናምናለን፤ ነፍሳችንና ሥጋችን አንድ ሆነው እንደሚነሡ እናምናለን፤ በመንግሥተ ሰማያት የዘላለም ሕይወት እንዳለ እናምናለን።

## በግእዝ

---

1) ነአምን በአሐዱ አምላከ አብ አኀዜ ኲሉ ዓለም፥ ገባሬ ኲሉ ዘያስተርኢ፥ ወኲሎ ዘኢያስተርኢ።

2) ወነአምን በአሐዱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወልደ እግዚአብሔር ዋሕድ፥ ዘተወልደ እምአብ ተወልደ ቅድመ እም ህላዌሁ ለአብ፥ ወበደኃሪ መዋዕል ተወልደ እም እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወእመንፈስ ቅዱስ። ኮነ ብእሴ ፍጹመ፥ ዘቦቱ ነፍስ፥ ወሥጋ፥ ወልቡና፥ ወአእምሮ፥ ወኲሉ ዘቦቱ ለሰብእ ዘእንበለ ኀጢአት። አኮ ውእቱ እምዘርዐ ብእሲ ወኢኀደረ ውስቴቱ ዘከመ ኲሉ ሰብእ፥ አላ ለሊሁ ነሥአ ሥጋ ሎቱ ለባሕቲቱ ወአስተፃመሮ በተዋሕዶ።

አኮ ከመ ኩሎሙ ነቢያት ዘሰፍሐ ቦሙ፥ ወተናገረ ውስቴቶሙ፥ አላ ሰብአ ፍጹመ ቃል ሥጋ ኮነ፥ ወኢተወለጠ፥ ወኢያፍለሰ መለኮቶ ኀበ ከዊነ ትስብእት፥ ወረሰየ ፍጻሜሁ ቅድስተ በብርሃን ምስለ መለኮት። አሐዱ ውእቱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ውእቱ እግዚእነ፥ ውእቱ ንጉሥ፥ ውእቱ ዘሞተ በሥጋ፥ ወተንሥአ፥ ወዐርገ ሰማያተ በዝንቱ አሐዱ አካል፥ ወካዕበ ይመጽእ በዝንቱ አሐዱ አካል።

3) ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ነባቢ በውስተ ሕግ፥ወሰባኪ በነቢያት፥ ዘወረደ በዮርዳኖስ፥ ወተናገረ በሐዋርያት፥ ወኅደረ በቅዱሳን፤ ወነአምን ቦቱ ከመ ውእቱ ህላዌ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም ጰራቅሊጦስ ዘኢተፈጥረ ዘሠረጸ እምአብ ወነሥአ እምወልድ። ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንተ ሐዋርያት።

4) ወአሐቲ ጥምቀት ለንስሓ፥ወለስርየተ ኀጢአት።

5) ወአሐቲ ትንሣኤ ለሙታን፥ ወተዋሕዶተ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንግሥተ ሰማያት። ወሕይወት ዘለዓለም።